MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

የወላጅ/ሞግዚት መመሪያ:-

# EXTENDED SCHOOL YEAR
# የተራዘመ የትምህርት አመት

# ESY

## አገልግሎቶች

የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ልዩ የትምህርት አገልግሎቶችን ለሚቀበሉ ተገቢ(ብቁ) ተማሪዎች የተራዘመ የትምህርት ዓመት (ESY) አገልግሎቶችን ይሰጣል። እነዚህ አገልግሎቶች በሰመር/summer ወቅት /በበጋ ወቅት/ የሚሰጡ ነፃ እና አግባብነት ያለው የህዝባዊ ትምህርት (FAPE) አካል ናቸው። ይህ መፅሄት የ ESY አገልግሎቶችንና የብቃት መስፈርቶችን እንድትገነዘቡ ለማገዝ የተዘጋጀ ነው።

Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

የልዩ ትምህርት ጽ/ቤት
Office of Special Education

## የተራዘመ የትምህርት ዓመት አገልግሎቶች ምንድን ናቸው?

የተራዘመ የትምህርት ዓመት (ESY) በአንድ ተማሪ ልዩ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ውስጥ የተካተቱ ግቦችና ዓላማዎችን ለመድረስ የተተለሙ ከመደበኛ የትምህርት ዓመት ባሻገር የልዩ አገልግሎቶች ልዩ ተቀጥያ ናቸው። ESY የትምህርት ዓመት ማርዘሚያ ማለት አይደለም፣ አውቶማቲክ /የበጋ ወቅት/ የሰመር/summer ት/ቤት ምደባ፣ ወይም ማበልጸጊያ/ ለማዳበሪያም አይደለም፤ ወይም ደግሞ እያንዳንዱ ስንክልና ያለው/ያላት ተማሪ ESY ያስፈልገዋል/ያስፈልጋታል ማለትም አይደለም። ሀቁ ግን፣ ESY ይልቁንም ስንክልና ላላቸው ለጥቂት ተማሪዎች ብቻ ተገቢ ሊሆን ይችላል።

## የ ESY ውሳኔዎች እንዴት ነው የሚከናወኑት?

ወላጅ/ሞግዚት፣ ተማሪ (አግባብነት ካለው)፣ የተማሪው(ዋ) መምህር/መምህራን፣ ተዛማጅ የአገልግሎት ሰጪዎች፣ እና አስተዳዳሪ/ተወካይ የሚያካትተው የ IEP ቡድን፣ ስለ ተማሪው(ዋ) ለ ESY አገልግሎቶች ብቁ መሆን/አለመሆንን ይወስናል።

## ESY ውሳኔዎች የሚሰጡት መቼ ነው?

በየዓመቱ በሚደረግ የግምገማ ስብሰባ ላይ ስፔሻል የትምህርት አገልግሎት ስለሚያገኝ/ስለምታገኝ ማንኛውም ተማሪ ለ ESY አገልግሎት ብቁ መሆን/አለመሆን የ ESY ቡድን የመመልከት እና የመገምገም ህጋዊ ግዴታ አለበት። በተማሪው/ዋ ፍላጎቶች መሰረት፣ የ ESY አገልግሎቶች በአይነት፣ በብዛት/ጥንካሬ፣ በቦታ፣ የተያያዙ አገልግሎቶችን በማካተት፣ እና በጊዜ ርዝመት ሊለያዩ ይችላሉ። ስለ ተማሪ መረጃ/ዳታ ግምገማ በሚደረግበት ወቅት የ ESY ቡድን ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ነገሮች ይመለከታል፡-

- ★ ወደነበረ(ች)በት መመለስ (መቀልበስ)/መተካት (Regression/Recoupment)
- ★ ያሳየው-ያሣየችው የለውጥ መጠን/ደረጃ
- ★ ብቅ ያሉ/የሚስተዋሉ ችሎታዎች/ጥሰው የሚወጡ እድሎች
- ★ ጣልቃ-ገብ ስነምግባር
- ★ የስንክልናው አፈጣጠር እና/ወይም ክብደት
- ★ ልዩ ሁኔታዎች

በትምህርት ዓመቱ ውስጥ ሊኖር የሚችለዉን የተማሪው(ዋ)ን የ ESY ፍላጎት በበቂ ሁኔታ ለማሳካት ገና መሆኑን የ IEP ቡድን ካመነበት ይህንን ውሳኔ ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ ይችላል። ውሳኔው የሚተላለፍ ከሆነ፣ የ IEP ቡድን የተማሪው(ዋ)ን የ ESY አገልግሎቶችን ፍላጎት ለመመልከት፣ ይግባኝ መጠየቅ ቢያስፈልግ ለወላጅ በቂ ጊዜ እንዲኖር ታሳቢ በማድረግ በቂ ጊዜ ተሠጥቶ በሌላ ጊዜ መሰብሰብ ይኖርበታል።

## የ ESY ብቃት እንዴት ነው የሚወሰነው?

ትኩረቱ *ትምህርታዊ ጠቀሜታዎችን በመጠበቅ እና FAPE ማጣት በሚያስከትለው ተጽእኖ ዙርያ ዋነኛ/ጥልቅ ችሎታዎች ላይ ያጠነጥናል። ESY ለመወሰን በተለይ የሚሰጥ ፎርሙላ የለም፣ ይልቁንም፣ ይህ ጥያቄ የበፊቱን ወደኋላ ተመልሶ በማሰብ እና ወደፊት ሲተነበይ በርካታ የመረጃ ነጥቦችን ማካተት አለበት። የ IEP ቡድን መረጃው በከፍተኛ ደረጃ የችሎታ ማሳጣትን ደረጃ እና ለረዥም ጊዜ ለአጠቃላይ ትምህርታዊ ግቦች እንቅፋት ስለመሆኑ እና ትምህርታዊ ጥቅሞችን በከፍተኛ ደረጃ የሚያሳጣ እንደሆነ መረጃዎቹ የሚያሟሉ መሆኑን በጥልቀት መገምገም ይጠበቅበታል።

* ዋና/አይነተኛ የህይወት ክህሎት-ችሎታ፣የማህበራዊ እና የስነባህርይ ችሎታዎች/ክህሎቶችን ጨምሮ፣ ለተማሪው(ዋ) አጠቃላይ ትምህርታዊ መሻሻል ወሳኝ ናቸው ተብለው በ IEP ቡድን የሚወሰኑ ማንኛውንም ክህሎት ያካትታል። ለተማሪው(ዋ) ልዩ ፍላጎቶች ወሳኝ/ዋና የሆኑ የህይወት ችሎታዎችን በመወሰን አኳያ፣ የትምህርት ቤት ዲቪዥን ተማሪው(ዋ) ራስን ችሎ ለመኖር፣ መጸዳጃ ቤት መጠቀም፣ ራስን መመገብ፣ ግንኙነት፣ ልብስ መልበስ፣ እና ሌሎችም ራስን ለመርዳት የሚያስችሉ ልዩ ክህሎቶችን ግምት ውስጥ ያስገባል። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ የትምህርት ቤት ዲቪዥን አካደሚያዊ እና የስነባህርይ ጉዳዮችን ሊመለከት እና ምላሽ ሊሰጥ ይችላል። የተማሪን እድሜ፣ ችሎታ፣ እና ትምህርት ቤት የተወ(ች)በትን ዓመት ቁጥር፣ ማንበብ፣ ሒሳብ፣ እና የጽሑፍ ቋንቋ የመሣሰሉት ወሳኝ የህይወት ክህሎት መሆኑን ታሳቢ ይደረጋል።

## የ ESY አገልግሎቶች እንዴት ይወሰናሉ?

ተማሪው/ዋ የ ESYን አገልግሎቶች ለመቀበል ተፈላጊዎቹን መስፈርቶች ያሟላል/ታሟላለች ብሎ የ IEP ቡድን ከወሰነ፣ በ ESY ወቅት መተግበር ያለባቸውን ያለባቸውን ግቦችንና አገልግሎቶችን ይለያሉ። የሚከተለው መረጃ በወቅታዊው IEP ተሰንዷል፡-

- ★ የ ESY አገልግሎቶች የሚፈልጉ የተወሰኑ ግቦችና አላማዎች።
- ★ የ ESY IEP ዓላማዎችን ለማሳካት የሚያስፈልጉ ዓይነት(ቶች)፣ መጠን/ብዛት(ቶች)፣ የሚወስደው ያክል ጊዜ፣ እና ትራንስፖርትን ጨምሮ ልዩ ትምህርትና የተያያዘ(ዙ) አገልግሎቶች።
- ★ የ ESY IEP ግቦችን ለመድረስና የ ESY አገልግሎቶችን ለመስጠት መለስተኛ/መጠነኛ ማእቀብ የሚደረግበት ሁኔታ።
- ★ ስንክልና ከሌላቸው እኩያዎቹ/እኩያዎቿ ጋር፤ ተማሪው/ተማሪዋ፤ የሚሳተፍበት/የምትሳተፍበት የጊዜ ብዛት/መጠን።

ወላጆች/ሞግዚቶች የ ESY አገልግሎቶችን የመቀበል ወይም ያለመቀበል መብት አላቸው። ወላጆች/ሞግዚቶች የ ESY አገልግሎቶችን የሚቀበሉ ከሆነ፣ ኬዝ ማናጀሩ(ሯ) የ ESY ምዝገባ ሂደትን ይሞላል/ትሞላለች፣ እና የሚቻል ከሆነ ለ ESY መጓጓዣ ያመቻቻል/ታመቻቻለች።

## ወላጆች/አሳዳጊዎች ከ IEP ቡድን ውሳኔ ጋር ካልተስማሙስ?

ወላጆች/አሳዳጊዎች በ IEP ቡድን አባልነታቸው ዋጋ ይሰጣቸዋል እናም በ ESY በልጃቸው/ተማሪያቸው ትምህርት ጉዳይ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ይሳተፋሉ። በ IEP ስብሰባ ወቅት፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች ስለ IEP እና ስለ ESY ኢንፎርሜሽን/መረጃዎችን ያገኛሉ። የ ESY ውሳኔ አጭር የፅሁፍ መግለጫ በተጨማሪ ይቀበላሉ። ወላጆች/አሳዳጊዎች በ IEP ቡድን ውሳኔ ካልተስማሙ፣ የአስተዳደራዊ ይግባኝ እንዲታይ፣ ለግልግል፣ ወይም በ 240-740-3230 ለ "Resolution and Compliance Unit" በመደወል በልዩ ትምህርት ህጋዊ ችሎት እንዲታይ መጠየቅ ይችላሉ።

## ወላጆች/ሞግዚቶች የበለጠ መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ የልዩ ትምህርት ጽ/ቤትን ለማግኘት ይችላሉ፡-

**የልዩ ትምህርት ጽ/ቤት**
Office of Special Education
240-740-3042

**የተራዘመ የትምህርት ዓመት አገልግሎቶች** (Extended School Year Services)
240-740-3855

**የተማሪ እና የቤተሰብ ድጋፍ እና ተሳትፎ ጽ/ቤት**

240-314-4824

### የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) የፀረ-መድሎ መግለጫ
### MCPS Nondiscrimination Statement

የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ዘርን፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ የዘር ሃረግ፣ የብሔር ማንነት፣ ኃይማኖት፣ የስደተኝነት ሁኔታ፣ ጾታ፣ ስነ-ጾታ፣ የጾታ ማንነት (gender identity)፣ የጾታ አገላለጽ (gender expression)፣ የጾታዊ ግንኙነት ዝንባሌ/ምርጫ (sexual orientation)፣ የቤተሰብ/የወላጆች የኑሮ ደረጃ/አቋም/ሁኔታ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ እድሜ፣ ድህነት፣ እና የማህበራዊ ኤኮኖሚያዊ አቋም፣ ቋንቋ፣ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳተኝነት፣ በህገመንግስት ጥበቃ የተደረገላቸው ሁኔታዎችን ባህሪያትን ወይም ተዛማጅነት ያላቸውን (affiliations) መሠረት ያደረገ ሕገ-ወጥ አድሎ/መድሎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፣ በሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነትን፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ፣ ሲደረግ የቆየ ትጋትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። አድልዎ የሚከተሉትን የተወሰኑ ምሳሌዎችን ያካትታል፡-ጥላቻ፣ ሁከት፣ ደንታቢስነት፣ ወከባ፣ ማስፈራራት፣ ማሸማቀቅ፣ ንቀት፣ ወይም ማጥቃት። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ደምብ/Policy ACA ስለ ጸረ-መድሎ፣ ፍትህ፣ የዳበረ ባህል ይመርምሩ። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ አስፈላጊ/ተፈላጊ መሆኑ(ኗ)ን፣ በተለይም የትምህርት ውጤቶች የሚረጋገጡት በምንም ዓይነት ግለሰብ ባለበት(ባለባት) ምክንያት ወይም ይሆናል ተብሎ የሚገመት ግላዊ ጠባዮች የሚተነበዩ አለመሆናቸውን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በቅድሚያ መወሰድ ስላለባቸው የፍትህ እርምጃዎች የተዛባ አመለካከትን፣ ማረጋገጫ የሌላቸው የማዳላት/ልዩነት አፈጻጸሞችን የሚያስከትሉትን አሉታዊነት፣ የትምህርት እና የሥራ መቀጠር እኩልነትን የሚያሰናክሉ መዋቅራዊ እና ድርጅታዊ አሠራር ደንቃራዎችን በተለይ ያስገነዝባል።

| በ MCPS ሰራተኛ* ላይ ስለደረሰ መድሎዎ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች ለማቅረብ | በ MCPS ተማሪዎች ላይ የአድልዎ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች ካላችሁ* |
|---|---|
| የሰራተኛ ተሳትፎ እና የሥራ ግንኙነት ጽ/ቤት<br>የአፈጻጸም እና የክትትል/የምርመራ መምሪያ<br>Department of Compliance and Investigations<br>850 Hungerford Drive, Room 55<br>Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>OCOO-EmployeeEngagement@mcpsmd.org | Office of the Chief of Staff<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 162<br>Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>COS–StudentWelfare@mcpsmd.org |

* ክትትል፣ ቅሬታ/ስሞታ፣ ወይም ስንክልና ላለባቸው ተማሪዎች አመቺ ስፍራ ለመጠየቅ፣ ወደ ልዩ ትምህርት ተቆጣጣሪ ጽ/ቤት፣ የቅሬታ ሰሚና መፍትሔ ሰጪ ን/ክፍል በ ስልክ ቁጥር 240-740-3230 ለቀርብ/ሊመራ ይችላል። ለሰራተኞች መገልገያዎች ወይም ማሻሻያዎች በሚመለከት የሚቀርቡ ጥያቄዎች ወደ Office of Employee Engagement and Labor Relations, Department of Compliance and Investigations/ የሰራተኛ ተሳትፎ እና የስራ ግንኙነት የአፈጻጸም እና የክትትል (የምርመራዎች) መምርያ፣ ስልክ፡- 240-740-2888 ሊመሩ ይችላሉ። በተጨማሪ፣ አድሎአዊነት ቅሬታዎች ለሌሎች ኤጀንሲዎችም ፋይል ሊደረጉ ይቻላል። እነርሱም፡- the U.S. Equal Employment Opportunity Commission, Baltimore Field Office, City Crescent Bldg, 10 S. Howard Street, Third Floor, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); ወይም U.S. Department of Education, Office for Civil Rights, Lyndon Baines Johnson Dept of Education Bldg., 400 Maryland Avenue, SW, Washington, DC 20202-1100, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህ ሠነድ ካስፈለገ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ከእንግሊዝኛ በሌሎች ቋንቋዎችና በሌላ አማራጭ ቅርፀት ሊገኝ ይችላል። በአካል ጉዳተኝነት ስለሚኖሩ አሜሪካውያን ደንብ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች ኮሙኒኬሽን ዲፓርትመንት/MCPS Department of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (ሜሪላንድ ማዞሪያ)፣ ወይም PIO@mcpsmd.org. የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚፈልጉ ግለሰቦች ወይም የንግግር ትርጉም/ምልክት አገልግሎት ለማግኘት የሞንትጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በስልክ ቁጥር፡- 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) ወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org መገናኘት ይችላሉ። የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS)፣ ወጣት ስካውቶችን (ወንድ/ሴት) እና ሌሎችም የሚመለከታቸውን ወጣት ቡድኖችን በእኩል ያስተናግዳቸዋል።

Maryland's Largest School District
**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

በመገልገያ እቃዎች/ቁሳቁሶች አስተዳደር መምሪያ ለኮንሶርሺያ ን/ክፍል የዝንባሌ ምርጫና ማመልከቻ ፕሮግራም አገልግሎት ታተመ
Department of Materials Management for the
Division of Consortia Choice and Application Program Services (DCCAPS)

0626.20ct • Editorial ፣ Graphics & Publishing Services • 10/19 • NP